የልማት ረጅዎች ቡድን መግለጫ

አዲስ አበባ

ህዳር 2 ቀን 1998 ዓ.ም.

የአውሮፓ ኅብረትና የአሜሪካ አምባሳደሮች ጥቅምት 27 ቀን 1998 ዓ.ም. ካወጡት መግለጫ ጋር በሚጣጣም መልኩ የልማት ረጅዎች ቡድን (DAG) በቅርቡ በኢትዮጵያ ውስጥ በአዲስ አበባና ሌሎች ሥፍራዎች የተፈጠረው ሕዝባዊ ሁከት ያስከተለው ሞትና የአካል ጉዳት ያሳደረበትን ጥልቅ የሆነ ሀዘን ይገልጻል፡፡

እነዚህ የፖለቲካ ሁከቶችና በአገሪቱ ቀጣይ ልማት ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ የልማት ረጅዎችን ቡድን ያሳስበዋል፡፡

የልማት ረጅዎች ተልዕኮ በኢትዮጵያ ቀጣይ ልማትን ማስፈን ነው፡፡ እነዚህ ሁከቶች በመንግሥትና በለጋሽ ማኅበረሰቦች በጋርዮሽ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሲገነባ የቆየውን የዕርዳታ እና የድህነት ቅነሳ ጥረት ያዳክሙታል፡፡ ይኸን ሁኔታ አስከፊ ከሆነው ድህነትና ከነዳጅ ዘይት ዋጋ ጋር በተላመደ እያንዣበበ ያለውን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር አዛምዶ ማየት ያሻል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የተነሳ አስተዋጽኦዎችን ውጤታማነት በሚኖረው አኳኋንና ያለምንም ወገናዊነት ለተረጅው ድሀ መድረሱን ለማረጋገጥ ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን የልማት ትብብር አፈጻጸም የልማት ረጅዎች ቡድን በአንድነት ሆኖ በመገምገም ላይ ነው፡፡

ጠንካራ የሆነ ዲሞክራሲን የእያንዳንዱን ዜጋ ሰብዓዊ መብት ከማክበር ጋር አጣምሮ ለመገንባት በጋርዮሽ በገባነው ግዴታ መሠረት፣ የልማት ረጅዎች ቡድን ለዲሞክራሲ እና ቀጣይ ልማት የተጠናከረ ተአማኒነት መኖር የሚበጅ የልማት ትብብር ለማፍለቅ እንዲቻል ለዚህ መሰናክል የሆኑትን ለመለየት ከመንግሥት እና ከቀሪትም ስጉዳዩ አግባብ ካላቸው ወገኖች ሁሉ ጋር እየሠራ ነው፡፡

የልማት ረጅዎች ቡድን (DAG) በኢትዮጵያ ውስጥ በአፍሪካ ልማት ባንክ (ADB)፣ ኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ካናዳ፣ እንግሊዝ፣ የአውሮፓ ማኅበረሰብ ልዑካ፣ ፊንላንድ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመንይ፣ አይርላንድ፣ ኢጣልያ፣ ጃፓን፣ ኔዘርላንድስ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድን፣ አሜሪካ እና የዓለም ባንክ የተወከለ ነው፡፡